## "ያድህነ እመዓቱ ይሰዉረነ በምህረቱ" !!! " ኢትዮጵያን የሚያዉኩ ጉዳዮች"

ገብርኤል ብዙነህ

የሀገራችንን ኢትዮጵያ አካል ቆርሶ ለሱዳን የሚሰጠው ውል አገራችንን ኢትዮጵያን የሚያወድም ነው። እንግሊዝ ሱዳንን በቅኝ ግዛት ይዛ በነበረችበት ወቅት፣ ሻለቃ ጉዌን በሚባለው መኮንኗ አማካኝነት እ.ኤ.አ. በ1902 ዓ .ም ድንበር ነው ብላ ያሰመረችውን መስመር እስከ ዛሬ ድረስ ኢትዮጵያ ውስጥ የፖለቲካ ሥልጣን የጨበጠ መንግሥት ያልተቀበለውንና ያለ ኢትዮጵያ ዕውቅና የተደረገ ህገ-ወጥና ጎጂ የድንበር መስመርን ነው ህወሓት የተቀበለው። ኢትዮጵያውያን ከማህዲስቶችና ከደርቡሾች ጋር በመዋጋት ከፍተኛ መስዋዕት ከፍለው ያቆዩትን፣የሀገራችንን መሬት ዘረኛው የወያኔ አምባገነን አገዛዝ ለሱዳን አሳልፎ ሲሰጥ ግን ኢትዮጵያዊያን በዝምታ የምናየው አይሆንም። 1200 ኪሎሜትር የኢትዮጵያን ለም፣ ውሃ-ገብና ደን-ለበስ የድንበር መሬት ለሱዳን የሚሰጠውን፣ በሀገር ጥቅም ላይ የተፈፀመ የክህደት ውል- የሱዳኑ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ዓሊ ካርቲ ኅዳር 24 ቀን 2006 ዓ. ም ካርቱም ውስጥ ታትሞ በወጣው፣ "ሱዳን ቪዥን" በሚባለው ዕለታዊ ጋዜጣ የነአቶ ኃይለማርያም ደሳለኝን ልዑክ ጉብኝት ጠቃሚነት ሲገልጽ፣ ሁለቱ መሪዎች የጋራ ድንበር ላይ የመስመር ቋሚ ምልክቶችን የማድረግ ተግባር እንዲፈጸም ያደርጋሉ ተብሎ እንደሚጠበቅ ገልጾ ስብሰባው ከተጠናቀቀ በኋላ ይህ ጉዳይ መፈጸሙን ሱዳናውያኑ አረጋግጠዋል።

የኢትዮጵያ መሬት  ዓለም ያስደመመ የመላው ዓለም የጀግንነት ልዩ መንፈስ የታሪክ ምሰሶ፣ ሰው የመሆን ምንጭ አምባና ማዕከል ነው። ይህ መሬታችን የቅዱስ ምድር የኤዶም ገነት ምድር ነው። የዚህ መሬታችን ባለቤትነት ባዕድነትን፣ ተስፋፊነትን ገፍትሮ በማቅለጥና በማውደም ለመሬቱ በመሬቱ ድልን በደሙ ያቀለመ ቀዳሚ የትውልድ ነጻ ኢትዮጵያዊ መሬታችን ነው። መሬታችን መገኛችን ነጻነታችን ነው። ነፃነታችን ኢትዩጵያዊነታችን ረቂቅ ነጻ ሰው የመሆን ቅኔ ነው። አፍንጫ አይን እንዳልሆነ ሁሉ የኢትዮጵያ መሬትም የሱዳን አይደለም። በህግ አምላክ ፈተና ከመፈጠሩ በፊት አሸንፈው የተፈጠሩ በመሪታችን ላይ ያለው ማንነታችን ኢትዮጵያዊነት ነውና ለዘላለም ይኖራል። ኢትዮጵያዊነት ተቀድቶ ያማያልቅ የኤዶም ገነት ነውና ለኢትዮጵያ የዜግነት ታሪካዊ ግዴታችንን እንወጣ። የምንሞተው አንዴ ነውና ለታሪክ የሚሆን ስራ ለመሥራት እንሽቀዳደም! ጊዜዉ አሁን ነው። ካለፈ በኋላ ችግር ነው። እንተባበር። "ያድህነ እመዓቱ ይሰዉረነ በምህረቱ"